አባ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

አሐዱ አምላክ

አሜን ።

በመላው ዓለም የምትገኙ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፥ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ፥ የክርስቶስ ቤተ ሰቦች ምእመናን ፥ ኢትዮጵያውን ሁሉ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው እግዚአብሔር በሰላም አደረሳችሁ ።

የሰውን ዘር ለማዳን ሰው ሁኖ የተገለጠው ወልደ አብ ወልደ ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትንና ሥላጣኑን ሽሮ ፣ መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል በኃይሉ ስለ ተነሣ እንኳን ደስ አላችሁ ። ትንሣኤ የሰው ልጆች ሁሉ የነጻነትና የድል በዓል ነው ። የሰው ልጅ ካመነ አሸንፎት የሚቀር እንደሌለ ክርስቶስ በትንሣኤው አሳይቶናል ። ሞትንም ማሸነፍ እንደሚቻል አረጋግጦልናል ። ክርስቶስ ለራሱ ብቻ አይደለም የተነሣ እኛንም አስነሥቶናል ። ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ። "ተንሥአ ወአንሥአ ኩሎ ሙታነ = ተነሣ ሙታንን ሁሉ አነሣ" እንዳለ ክርስቶስ ሞትን ድል ነሥቶ ተነሥቷል። በአዳም ኃጢአት ፣ ሞት የገዛውን የሰው ልጅ ባሕርይም አስነሥቶታል ።

ትንሣኤውም የእግዘአብሔር ኃይል የተገለጠበት ፣ ጠላት ዲያብሎስ ድል የተናሣበት ፣ የሰው ልጅ ከማእሰረ ኃጢአት የተፈታበትና የዳነበት የነጻነትና የድል በዓል ነው ። በሰሙነ ትንሣኤ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ እያለች ትዘምራለች ፤ "ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን አሰሮ ለሰይጣን አግአዞ ለአዳም ፤ ሰላም እም ይእዜሰ ይኩን ሰላም = ክርስቶስ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፣ ሰይጣንን አሰረው ፤ አዳምን ነጻ አወጣው ፤ ከዛሬ ጀምሮ ፍጹም ሰላም ይሁን" ። ማለት ነው ። ይህም ክርስቶስ በሞቱ ሞትን ደምስሶ ፣ መልአከ ሞትን ከሥልጣኑ ሽሮ መነሣቱን እያሰበች ቤተ ክርስቲያን የምታሰማው የድል ዜማ ነው ።

የሰውን ልጅ ያዋረደውን ሞትን ረግጦት በመነሣቱ ቤተ ክርስቲያን በደስታ ትንሣኤውን ታከብራለች ። እንዲህም እያለች ትዘምራለች ። "ክርስቶንስ ተንሥአ እሙታን ፣ ሞተ ወኬዶ ለሞት ፣ ለእለ ውስተ መቃብር ወህበ ሕይወተ ዘለዓለም ዕረፍተ = ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፣ ሙቶ ሞትን ረገጠው ፤ በመቃብር ውስጥ ላሉት ሁሉ ሕይወትን ሰጠ ።" ትላለች ።


15521 Orchard Run Drive, Bowie, MD 20715 Phone:(301) 262-3031

የትንሣኤ በዓል የተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚያከብሩት በዓል አይደለም ። የሰው ልጅ ሁሉ በደሙ ተቀድሶ የሚያከብረው የሰው ዘር ሁሉ የነጻት በዓል ነው እንጂ ።

ስለዚህም ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ይላል “ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ = ምድርም በክርስቶስ ደም ታጥባ ፋሲካን ታከብራለች” ማለት ነው ። ስለዚህ ትንሣኤውን በፍጹም ደስታ ልናከብር ይገባል ።

**በመላው ዓለም የምትገኙ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ ሆይ !!**

ትንሣኤ ሁለት ወገን ነው ። አንደኛው ትንሣኤ ልቡና ይባላል ። ሁለተኛው ትንሣኤ ሥጋ ይባላል ። ትንሣኤ ልቡና የሚባለው ዛሬ በክርስቶስ ያመኑ ፥ ለእነውት የቆሙ ፣ ለፍትሕ ለርትዕ የተነሡ ፥ ለመልካም ሥራ የተሰለፉ ሁሉ የሚኖሩበት ሕይወት ትንሣኤ ልቡና ይባላል።

ሁለተኛውን የሥጋ ትንሣኤ ደግሞ ጌታችን ዳግመኛ ሲመጣ እንነሣለን ። ጌታ የተነሣ እኛን ሊያስነሣ ነውና ። እኛም ዛሬ በእውነት ለእውነት ልንነሣ ይገባል ። ዛሬ የመድኃኒታችንን ትንሣኤ ስናከብር ሁላችንም ለሰላም በአንድነት ልንነሣ ይገባል ። ጌታ ስለ እኛ እንደ ተነሣ ፣ እኛም ለተጠቁት ፥ ለተረገጡት ፥ ነጻነት ላጡት ፥ የሞት ጥላ ላጠላባቸው ልንነሣላቸው ይገባል ። ዛሬ ለሕዝባችን የሚያስፈለገው እውነተኛ ትንሣኤ ልቡና ነው ። ለሀገራችንም የአንድነትና የሰላም ትንሣኤ ያስፈልጋታል ። አገራችንን ከልዩ ልዩ ችግር ለማዳን አንድ ሁነን ልንነሣ ይገባል ። የሞት ያህል ለሕዝባችን የከበደውን ልዩነት አሸንፈን ለአንድነትና ለፍቅር ልንነሣ ይገባል ።

ሞትን ድል ነሥቶ ለተነሣው ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ይሁን ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ ይቀድስ ።

ሕዝባችን ተበትኖ የሚኖርበትን መላውን አህጉር ሁሉ እግዚአብሔር ይባርክ።

እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሣችሁ ። አሜን።

አባ መርቆሬዎስ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ።

መርቆሬዎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA